# <u>አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ)</u>
# <u>የተሻሻለ- የመመስረቻ ፅሁፍ</u>

## ክፍል አንድ፡-<u> ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### <u>መቅድም፡-</u>

እኛ ስማችንና ፊርማችን በዚህ የመመሥረቻ ፅሁፍ አባሪ እና አካል በሆነው የባለአክሲዮኖች 8ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የመገኘት ወረቀት (Attendance Sheet) ላይ የሰፈረው የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ባለ አክሲዮኖች፡-

- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 307/2/ እና 316 የመድን ሥራ ፍቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 መሠረት የማህበሩ ሕግ እንዲሆን በተዘጋጀው የመመሥረቻ ፅሑፍና ከጽሑፉ ጋር በተያያዘው የመተዳደሪያ ደንብ ላይ በፈረሙ፣ 30,000.00 የተፈረሙ አክሲዮኖች (30,000,000.00 ብር የተፈረመ ዋና ገንዘብ) ባዋጡ እና ዋና ገንዘቡን 1/4ኛ (25%) በጥሬ ገንዘብ በከፈሉ አምስት ባለ አክሲዮኖች ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም የተቋቋመ መሆኑን በመገንዘብ፣
- ማህበሩ ከተቋቋመ በኋላ በነበሩት በርካታ ዓመታት ውስጥ ከተፈረሙና ከተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት መጨመር፣ ከማህበርተኞች ቁጥር መጨመር፣ ከኩባንያው የንግድ ዓላማና የሥራ ዘርፍ መስፋት ጋር ተያይዞ የታዩ ለውጦችን ባገናዘበ መልኩ በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ ማለትም እንደየ ቅደም ተከተላቸው መስከረም 28 ቀን 1991 ዓ.ም፣ ታህሳስ 7 ቀን 2003 ዓ.ም፣ ታህሳስ 6 ቀን 2005 ዓ.ም፣ ታህሳስ 18 ቀን 2007 ዓ.ም፣ ህዳር 18 ቀን 2008 ዓ.ም እና ታህሳስ 4 ቀን 2012 ዓ.ም በተካሄዱ 2ኛ፣3ኛ፣4ኛ፣5ኛ፣6ኛ እና 7ኛ የባለ አክሲዮኖች ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች ውሳኔዎች መሠረት በመመሥረቻ ጽሑፍና በመተዳደሪያ ደንቡ የተወሰኑ አንቀጾች ላይ ማሻሻያዎች የተደረጉ መሆኑን በመገንዘብ፣
- በአጠቃላይ ማህበሩ በየወቅቱ የደረሰባቸውን የዕድገት ደረጃዎችና በየጊዜው የተደረጉ ለውጦችን ባገናዘበ መልኩ በነባሩ የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ የተወሰኑ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያዎች የተደረጉ ቢሆንም፣ ነባሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ ሙሉ በሙሉ ያልተተካ መሆኑን በመገንዘብ፣
- የማህበሩ የመመሥቻ ጽሑፍ ማህበሩ አሁን የደረሰበትን አጠቃላይ የእድገት ገጽታ በተለይም የተፈረሙ አክሲዮኖች ብዛት 357,897.00፣ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ብር 357,897,000.00 (ሶስት መቶ ሃምሣ ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ ብር)፣ የተከፈለ ካፒታል ብር

275,946,000 (ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ብር)፣ የማህበሩ አባላት ብዛት 308 መድረሱን በትክክል በሚያንፀባርቅ መልኩ፣ እንዲሁም በ2013 ዓ.ም ከወጣው አዲስ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 255 እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች የሕግ፣ የደንብ ወይም የመመሪያ ድንጋጌዎችንም ባገናዘበ መልኩ መሻሻል ያለበት መሆኑን በማመን፣

- ይህ ዛሬ ታህሳስ 15 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደው የባለ አክሲዮኖች 8ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በንግድ ሕግ አንቀጽ 400(1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የቀድሞው የማህበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እንዲሁም የመተዳደሪያ ደንቡ ተሰርዘው በዚህ በተሻሻለው የመመሥረቻ ጽሑፍ እንዲተኩ በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

## **<u>አንቀፅ 1. የማህበሩ ስም</u>**

የማህበሩ ስም “አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር” ነው፡፡

# አንቀፅ 2. ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፎች

1. የማህበሩ ዋና መ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡
2. ማህበሩ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ በየትም ቦታ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

   2.1 የሚከተሉት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የማህበሩ ቅርንጫፎች ናቸው

**በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ**

1. ዋና መ/ቤት ቅርንጫፍ
2. ፍልውሃ ዓብይ ቅርንጫፍ
3. ዮሴፍ ቅርንጫፍ
4. ተ/ሃይማኖት ቅርንጫፍ
5. ሕይወት ቅርንጫፍ
6. አራዳ ቅርንጫፍ
7. ቂርቆስ ቅርንጫፍ
8. ጎፋ ቅርንጫፍ
9. ቦሌ/የካ ቅርንጫፍ
10. ገርጂ ቅርንጫፍ
11. አራት ኪሎ ቅርንጫፍ
12. መሰለሚያ ቅርንጫፍ
13. ቃሊቲ ቅርንጫፍ
14. ልደታ ቅርንጫፍ
15. አየር ጤና ቅርንጫፍ
16. ራስ ደስታ ቅርንጫፍ
17. ፊት በር ቅርንጫፍ
18. መስቀልፍላወር ቅርንጫፍ
19. መካኒሳ ቅርንጫፍ
20. ላም በረት ቅርንጫፍ
21. ስቴዲየም ቅርንጫፍ
22. ሲኤምሲ ቅርንጫፍ

**በክልል ከተሞች የሚገኙ**

23. ሃዋሳ ቅርንጫፍ
24. አዳማ ቅርንጫፍ
25. ጎንደር ቅርንጫፍ
26. ባህርዳር ቅርንጫፍ
27. ድሬዳዋ ቅርንጫፍ
28. መቀሌ ቅርንጫፍ
29. ደሴ ቅርንጫፍ
30. ጅማ ቅርንጫፍ
31. ወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ
32. ነቀምት ቅርንጫፍ
33. ሽሬ ቅርንጫፍ
34. ደብረ ብርሃን ቅርንጫፍ
35. አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ
36. ጅግጅጋ ቅርንጫፍ

3. ማህበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ መቼ እና የት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እንደሚያቋቁም የመወሰን ስልጣን የማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ ይሆናል፡፡

# አንቀፅ 3 -የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ፡፡

3.1 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የተዘረዘሩት የማህበሩ አባላት በሙሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ናቸው

3.2 የማህበሩ አክሲዮኖች በሙሉ እያንዳንዳቸው ላይ የተፃፈ ብር 1000.00 የአቻ ዋጋ (Par Value) ያላቸው ተራ የተመዘገቡ አክሲዮኖች ናቸው፡፡

3.3 የባለአክሲዮኖችና የአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡ (ከአክሲዮኖች ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ዝርዝርዝ መግለጫዎች በክፍል ሁለት -ንዑስ ክፍል 1-ቀርቧል፡፡)

| ተ.ቁ | የባለአክስዮን ስም | የባለአክስዮን | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የተፈረመ አክስዮን መጠን | የተከፈለ ገንዘብ መጠን | ያልተከፈለ ገንዘብ መጠን | አድራሻ<br>ከተማ |
| **ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች(Influential Shareholders')** | | | | | |
| 1 | ወጋገን ባንክ አ.ማ | 18,000 | 15,798,000 | 2,202,000 | አ.አ |
| 2 | አዲስ የመለዋወጫ እቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክስዮን ማህበር | 18,000 | 15,798,000 | 2,202,000 | አ.አ |
| 3 | ሕይወት እርሻ ሜካናይዜሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | 18,000 | 13,528,000 | 4,472,000 | መቐለ /አ.አ |
| 4 | መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂ. ኃ/የተ/የግ/ማ | 18,000 | 13,528,000 | 4,472,000 | መቐለ /አ.አ |
| 5 | አልመዳ ጨርቃጨርቅ ኃ/የተ/የግ/ማ | 18,000 | 13,528,000 | 4,472,000 | አድዋ/አ.አ |
| 6 | ሣባ እምነበረድ ኃ/የተ/የግ/ማ | 18,000 | 13,528,000 | 4,472,000 | አድዋ/አ.አ |
| 7 | አቶ አስመላሽ ምናዬ | 18,000 | 12,051,000 | 5,949,000 | አ/አ |
| 8 | ቱምሣ እንዶዉመንት | 18,000 | 11,250,000 | 6,750,000 | አ/አ |
| 9 | ወንዶ ኃ/የተ/የግ/ማ | 18,000 | 11,250,000 | 6,750,000 | አ.አ |
| 10 | ቱሬ ኃ/የተ/የግ/ማ | 17,300 | 14,058,000 | 3,242,000 | አ/አ |
| 11 | የትእማት ኢንቨስትመንት ማእከል (ኢፈርት) | 16,560 | 12,446,000 | 4,114,000 | መቐለ |
| 12 | ንጋት | 16,384 | 10,846,000 | 5,538,000 | ባህርዳር |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 13 | አቶ አለሙ በርሄ ተስፋ | 15,720 | 13,138,000 | 2,582,000 | አ/አ |
| 14 | ወ/ሮ ሃና ገ/መድህን ስብሀቱ | 14,564 | 9,641,000 | 4,923,000 | አ/አ |
| 15 | አቶ መሃመድ አብደላ ቃሲምና ወ/ሮ አስቴር ረታ | 10,200 | 6,753,000 | 3,447,000 | አ.አ |
| 16 | ብ/ጀ ሰለሞን በየነ ዳንጉል | 10,200 | 7,230,000 | 2,970,000 | አ/አ |
| 17 | ወ/ሮ ሰላማዊት ፍልፍሌ | 7,280 | 4,820,000 | 2,460,000 | አ/አ |
| **ድምር** | | **270,208** | **199,191,000** | **71,017,000** | |

## ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች (Non Influential Sahareholders')

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 18 | አቶ ሃሩን ያሲን አብዶ | 6,600 | 6,600,000 | - | አ/አ |
| 19 | አቶ ጌትነት ሽቴ | 6,215 | 6,215,000 | - | አ/አ |
| 20 | አቶ ዳንኤል መብራቱ | 3,672 | 3,222,000 | 450,000 | አ/አ |
| 21 | አቶ ብርሃኔ ግደይ መሸሻ | 3,200 | 2,808,000 | 392,000 | አ/አ |
| 22 | ወ/ሮ አዎ መሐመድ አብዱላሂ ኦግሰዴ | 3,101 | 3,101,000 | - | ድሬዳዋ |
| 23 | አቶ ገብሩ በየነ ንጉሴ | 3,000 | 1,875,000 | 1,125,000 | አ/አ |
| 24 | አቶ ሙሴ ዳዊት ገ/ጻድቅ | 2,250 | 1,974,000 | 276,000 | አ/አ |
| 25 | ወ/ት ብሩክታዊት ዳዊት ገ/ፃዲቅ | 2,250 | 1,974,000 | 276,000 | አ/አ |
| 26 | አቶ ብሩክ ዳዊት ገ/ፃዲቅ | 2,250 | 1,974,000 | 276,000 | አ/አ |
| 27 | አቶ ማህደር ዳዊት ገ/ፃዲቅ | 2,250 | 1,974,000 | 276,000 | አ/አ |
| 28 | ጣና ኮምዩኒኬሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | 2,110 | 1,586,000 | 524,000 | ባህርዳር |
| 29 | ሐጂ መሐመድ አብደላ ኦግሰዴ የንግድ ሥራዎች ኃ/የተ/የግ/ማ | 2,000 | 1,506,000 | 494,000 | ድሬዳዋ |
| 30 | አቶ ሽቴ ልኡልሰገድ | 1,820 | 1,205,000 | 615,000 | አ/አ |
| 31 | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ.የግ.ማ | 1,820 | 1,205,000 | 615,000 | አ/አ |
| 32 | መይሱን ሰኢድ ዳምጠዉ | 1,820 | 1,205,000 | 615,000 | አ.አ |
| 33 | ወ/ሪት ሂበ ሰኢድ መሃመድ እና ሌሎች ህጋዊ ወራሾች | 1,162 | 770,000 | 392,000 | ድሬዳዋ |
| 34 | አቶ የማነ ግርማይ ብስራት | 1,100 | 1,100,000 | - | አ/አ |
| 35 | አቶ ዮሴፍ አሰፋ ደበላ | 1,016 | 1,016,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 36 | አቶ ሀብታሙ ምስጋናው | 1,000 | 1,000,000 | - | አ/አ |
| 37 | ወ/ሮ መቅደስ ገ/ፃድቅ ገ/ዮሃንስ | 1,000 | 728,000 | 272,000 | አ/አ |
| 38 | አቶ አስመላሽ ተክሌ ገብሩ | 1,000 | 700,000 | 300,000 | አ/አ |
| 39 | ወ/ሮ ሰርካለም ሞላ ላቀው | 1,000 | 625,000 | 375,000 | አ/አ |
| 40 | አቶ መንግስቱ ሲያባራ | 908 | 602,000 | 306,000 | አ/አ |
| 41 | አቶ ማሩ እንዳላማው | 808 | 502,000 | 306,000 | ባህርዳር |
| 42 | አቶ ኃምዛ ሞኃመድ ሼክ | 600 | 440,000 | 160,000 | አ/አ |
| 43 | አቶ ወሂብ መሃመድ ቱሬ | 560 | 491,000 | 69,000 | አ/አ |
| 44 | አቶ ተስፋዬ ጎበና ተሊላ | 400 | 250,000 | 150,000 | አ/አ |
| 45 | ወ/ሮ ፈርዶስ አዱስ | 380 | 295,000 | 85,000 | አ/አ |
| 46 | ወ/ሮ ገነት አራጋው ገ/ማርያም | 378 | 378,000 | - | አ/አ |
| 47 | ወ/ሮ ኢየሩሳሌም ተፈራና/ካፒቴን አምሃ ቀፀላ | 364 | 241,000 | 123,000 | አ/አ |
| 48 | ወ/ሪት ሰውነት ሳሙኤል አለማየሁ | 364 | 241,000 | 123,000 | አ/አ |
| 49 | አቶ ብርሃኑ ታደሰ ጎጂው | 336 | 251,000 | 85,000 | አ/አ |
| 50 | ወ/ሮ አዜብ በየነ ሃጎስ | 334 | 212,000 | 122,000 | አ/አ |
| 51 | አቶ ገ/ህይወት ብርሃኔ ኃ/ማርያም | 300 | 188,000 | 112,000 | አ/አ |
| 52 | አቶ ደባልቀው ወ/ሚካኤል | 268 | 180,000 | 88,000 | አ/አ |
| 53 | አቶ ይልቃል መኮንን ምህረቴ | 268 | 195,000 | 73,000 | አ/አ |
| 54 | አቶ አንተነህ ሙሉጌታ አየለ | 264 | 264,000 | - | አ/አ |
| 55 | ወ/ሮ ሃናን መሃመድ አብዱርሃማን | 260 | 228,000 | 32,000 | አ/አ |
| 56 | ወ/ሪት ሜሮን ሰለሞን አፈሩ | 236 | 177,000 | 59,000 | አ/አ |
| 57 | አቶ ሳህለማርያም ደጀኔ ውለታው | 236 | 180,000 | 56,000 | አ/አ |
| 58 | ወ/ት ኢማን አህመድ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 59 | አቶ አብዱራህማን አብዱልባቂ ሙዲር | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 60 | አቶ ዳዊት አራጋው መክረጅ እና ወ/ሮ ኢየሩሳሌም ታደሰ ካሳ | 200 | 175,000 | 25,000 | አ/አ |
| 61 | አቶ ፈቃዱ ጴጥሮስ ገ/መስቀል | 200 | 175,000 | 25,000 | አ/አ |
| 62 | አቶ ደሳለኝ ሲማ ከሬባ | 200 | 125,000 | 75,000 | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 63 | አቶ አህመድ ኢብራሂም መሃመድ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 64 | አቶ ሙሉጌታ በቀለ ደረሰ | 200 | 125,000 | 75,000 | አ/አ |
| 65 | ወ/ት ቤዛ ጌታቸው | 184 | 184,000 | - | አ/አ |
| 66 | አቶ ካህሳይ አብረሃ ተስፋዬ | 184 | 138,000 | 46,000 | አ/አ |
| 67 | አቶ ሞልቶት አብዩ አግቦ | 184 | 134,000 | 50,000 | አ/አ |
| 68 | ወ/ሮ መሰብወርቅ ተበጀ ጸሃዬ | 168 | 168,000 | - | አ/አ |
| 69 | አቶ በለጠ አበበ ደምሴ | 164 | 110,000 | 54,000 | ድሬዳዋ |
| 70 | አቶ ታደሰ ወ/መድህን ተክሌ | 160 | 140,000 | 20,000 | አ/አ |
| 71 | አቶ ቴዎድሮስ ገ/እግዚአብሔር | 136 | 118,000 | 18,000 | አ/አ |
| 72 | አቶ ገረመው ልየው ተመስገን | 108 | 72,000 | 36,000 | ባ/ዳር |
| 73 | ወ/ሪት ማህደር መንግስቱ ይሄይስ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 74 | ወ/ሮ አምሳል ካሳሁን ሙላት | 100 | 87,000 | 13,000 | አ/አ |
| 75 | አቶ ፀጋዬ ጉደታ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 76 | ወ/ሪት ሄለን ፋሲል አባገና | 100 | 76,000 | 24,000 | አ/አ |
| 77 | አቶ አስናቀ እርቁ አበበ | 98 | 66,000 | 32,000 | አ/አ |
| 78 | ወ/ሮ አለምነሽ የኋላወርቅ ፈለቀ | 88 | 60,000 | 28,000 | አ/አ |
| 79 | ወ/ሮ ሰላም ገመቹ ሙካ | 88 | 60,000 | 28,000 | አ/አ |
| 80 | አቶ ፍፁም ሺፈራው ተከተለው | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 81 | ወ/ሮ ትርሃስ አባዲ ወ/ኪዳን | 80 | 80,000 | - | አ/አ |
| 82 | አቶ ሃ/ገብርኤል ሃ/ሚካኤል ወ/ፃድቅ | 72 | 50,000 | 22,000 | አ/አ |
| 83 | አቶ ፈዬ ቶቾ ኩራ | 68 | 59,000 | 9,000 | አ/አ |
| 84 | ወ/ሪት ማርታ ሃይሌ | 60 | 46,000 | 14,000 | አ/አ |
| 85 | አቶ ሺመልስ ሃይሉ ተቻነ | 56 | 41,000 | 15,000 | አ/አ |
| 86 | ወ/ሮ ዊንታ ዳዊት | 52 | 36,000 | 16,000 | አ/አ |
| 87 | አቶ አብይ አሰፋ ሊካሳ | 52 | 36,000 | 16,000 | አ/አ |
| 88 | አቶ ብስራት ጉግሳ አባተ | 52 | 36,000 | 16,000 | አ/አ |
| 89 | አቶ ጌታሁን አባተ ዳንጉል | 51 | 51,000 | - | አ/አ |
| 90 | አቶ ሺፈራው ጃርሶ | 50 | 50,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 91 | ዶ/ር ቶላ በሪሶ | 50 | 50,000 | - | አ/አ |
| 92 | ወ/ሪት መአዛ ፍሰሃ እሸቴ | 48 | 33,000 | 15,000 | አ/አ |
| 93 | ወ/ሮ ቤተልሄም ብርሃኑ | 46 | 30,000 | 16,000 | አ/አ |
| 94 | አቶ ሁሉንየሁ ለማ ገ/መስቀል | 42 | 40,000 | 2,000 | አ/አ |
| 95 | ወ/ሮ መውደድ እውቀቱ መኮንን | 40 | 40,000 | - | ደሴ |
| 96 | አቶ አቤል ፋንታሁን በትሩ | 40 | 40,000 | - | አ/አ |
| 97 | አቶ ረጋ አለማየሁ ሉለ | 40 | 40,000 | - | አ/አ |
| 98 | አቶ ቢንያም ታጠቅ | 38 | 33,000 | 5,000 | አ/አ |
| 99 | አቶ ሚካኤል ገ/እግዚአብሄር ገ/አረጋዊ | 36 | 24,000 | 12,000 | አ/አ |
| 100 | አቶ እዬብ ወዳጄነህ | 36 | 24,000 | 12,000 | አ/አ |
| 101 | ወ/ሮ ማህሌት ፍቃዱ | 36 | 24,000 | 12,000 | አ/አ |
| 102 | ወ/ሮ ሜቲ ታደለ | 32 | 20,000 | 12,000 | አ/አ |
| 103 | አቶ ሀይሉ ሞገስ ተ/ማርያም | 30 | 30,000 | - | አ/አ |
| 104 | ወ/ሪት ቤተልሄም ታደሰ | 28 | 20,000 | 8,000 | አ/አ |
| 105 | ወ/ሮ እንወይ ገ/መድህን | 224 | 224,000 | - | አ/አ |
| 106 | አቶ ብሩክ ዘመላክ | 20 | 17,000 | 3,000 | አ/አ |
| 107 | አቶ ጌታቸው አባተ መካሻ | 16 | 12,000 | 4,000 | አ/አ |
| 108 | አቶ ኪ/ማርያም መገርሳ ከነ | 16 | 12,000 | 4,000 | አ/አ |
| 109 | ወ/ሮ ምንትዋብ ይርጋለም | 12 | 12,000 | - | ሻሸመኔ |
| 110 | ወ/ሮ ሰናይት አየለ በላይ | 10 | 6,000 | 4,000 | አ/አ |
| 111 | አቶ ኑሩ ካሳው መሀመድ | 11 | 11,000 | - | ደሴ |
| 112 | ወ/ሪት ማርታ አማረ አለሙ | 10 | 10,000 | - | አ/አ |
| 113 | አቶ ኪሮስ ጂራኔ ደጋጋ | 984 | 729,000 | 255,000 | አ/አ |
| 114 | አቶ ካሳሁን በጋሻው ወግደረስ | 400 | 300,000 | 100,000 | አ/አ |
| 115 | አቶ ዳንኤል ተ/ብርሃን ገ/ኪዳን | 336 | 336,000 | - | አ/አ |
| 116 | አቶ ዮሃንስ ሃይሉ ፀሃዬ | 336 | 336,000 | - | አ/አ |
| 117 | አቶ ጌታቸው ለገሰ ጃሬ | 350 | 350,000 | - | አ/አ |
| 118 | አቶ ቴዎድሮስ ነጋ ገ/ሂወት | 268 | 268,000 | - | ትግራይ/ መቐለ |
| 119 | አቶ ደምስ አበራ ወ/ሰንበት | 400 | 400,000 | - | አ/አ |
| 120 | አቶ መዝሙር ሃዋዝ ሙላት | 268 | 268,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 121 | አቶ አብዱልናስር አማን ኮሚ | 268 | 268,000 | - | አ/አ |
| 122 | ወ/ሮ ቀለመወርቅ ታደሰ መታፈሪያ | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 123 | አቶ አስፋው ጌታቸው ክፍሌ | 236 | 236,000 | - | አ/አ |
| 124 | አቶ አበበ አስግዶም ታረቀ | 236 | 173,000 | 63,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 125 | አቶ በድሉ መኮንን እንግዳ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 126 | አቶ ተስፋዬ ግርማ ጁፋር | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 127 | አቶ ደጀኔ መገርሳ ኢድዬ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 128 | ወ/ሪት ንግስቲ መሃሪ ገ/ስላሴ | 220 | 220,000 | - | አ/አ |
| 129 | ወ/ሪት ሂሩት ገብረእየሱስ ዳዲ | 220 | 220,000 | - | አ/አ |
| 130 | ወ/ሮ ሂወት ሺገድብ መልካሙ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 131 | ወ/ሮ ሂሩት ነጋሽ ተሰማ | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 132 | አቶ አብነት መሸሻ በቀለ | 250 | 250,000 | - | አ/አ |
| 133 | አቶ ያብባል ዘውዴ ገ/እግዚአብሄር | 394 | 394,000 | - | አ/አ |
| 134 | አቶ ሲሳይ ተካ ታደገ | 350 | 350,000 | - | አ/አ |
| 135 | ወ/ሮ ደስታለም ለምለም ካህሳይ | 292 | 292,000 | - | አ/አ |
| 136 | ወ/ሮ ገነት መኩሪያ አበበ | 292 | 292,000 | - | አ/አ |
| 137 | ወ/ሮ ፍቅሬ ወልዱ ወንድሙ | 292 | 292,000 | - | አ/አ |
| 138 | አቶ ገ/ስላሴ ገ/መድህን ወ/ገብርኤል | 184 | 161,000 | 23,000 | አ/አ |
| 139 | አቶ መሃመድ ይስሃቅ ጀማል | 184 | 134,000 | 50,000 | አ/አ |
| 140 | አቶ ደረጀ ጌታቸው አለሙ | 184 | 184,000 | - | አ/አ |
| 141 | አቶ ሚካኤል መስፍን አጎናፍር | 174 | 159,000 | 15,000 | አ/አ |
| 142 | ወ/ሮ እየሩስአሌም ታደሰ ካሳ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 143 | ወ/ሮ ፍሬሂወት ገ/ዮሃንስ ገ/ህይወት | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 144 | ወ/ሮ አለም ታምሩ ያደቴ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 145 | ወ/ሮ ሰፊያ መሃመድ ሰኢድ | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 146 | ወ/ሮ ማስረሻ አበበ አባተ | 318 | 318,000 | - | አዋሳ |
| 147 | ወ/ሪት የሺወርቅ አስማረው ንጉሴ | 254 | 254,000 | - | አ/አ |
| 148 | ወ/ሮ ቆንጂት ከበደ ሀ/ማርያም | 168 | 168,000 | - | አዳማ |
| 149 | ወ/ሪት ራሄል አበራ ገዛኸኝ | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 150 | ወ/ሮ ሂሩት ሺፈራው ተበጀ | 368 | 368,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 151 | አቶ የማነ ብርሃን ገ/ማርያም | 148 | 109,000 | 39,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 152 | ወ/ሮ ሄለን ፋንታዬ ደምሴ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 153 | ወ/ሮ አይናዲስ ግርማይ ቸኮል | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 154 | ወ/ሮ ሰመሃል ገ/እግዚአብሄር ወ/አረጋይ | 234 | 234,000 | - | አ/አ |
| 155 | ወ/ሮ ሂወት ይስሃቅ ነጋሽ | 155 | 155,000 | - | አ/አ |
| 156 | ወ/ሮ ምስራቅ ዘውዴ አርቂ | 300 | 300,000 | - | አ/አ |
| 157 | ወ/ሮ ትብለጽ በየነ ተድላ | 169 | 169,000 | - | አ/አ |
| 158 | አቶ ተሰማ ህደቱ ዳቱ | 130 | 130,000 | - | አ/አ |
| 159 | ወ/ሮ መሰረት ደመላሽ ከበደ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 160 | አቶ ተፈረ አሰፋ አባተ | 270 | 270,000 | - | ደሴ |
| 161 | ወ/ሮ ራሄል እንዳለ ገ/ህይወት | 180 | 180,000 | - | አ/አ |
| 162 | አቶ ሞሲሳ ዲንሳ ሰርቤሳ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 163 | ወ/ሮ ገነት ዘካርያስ ተፈራ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 164 | ወ/ሮ አስቴር አበበ አያኖ | 180 | 180,000 | - | አ/አ |
| 165 | ወ/ሮ ሳራ ማሞ አጋፋው | 200 | 200,000 | - | ድሬዳዋ |
| 166 | አቶ ሰለሞን አስማረ አይቼህ | 100 | 100,000 | - | ጎንደር |
| 167 | ወ/ሮ ትዝታ ለገሰ አልማው | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 168 | ወ/ሮ መርሃዊት ፋንታሁን በላቸው | 100 | 73,000 | 27,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 169 | አቶ ሱራፌል ሙሉጌታ ሹምዬ | 100 | 73,000 | 27,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 170 | አቶ አሰፋ ግደይ አብረሃ | 100 | 73,000 | 27,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 171 | ወ/ሮ ደስታ መስፍን አልታዬ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 172 | አቶ አለምሰገድ መረሳ ፍስሀ | 88 | 60,000 | 28,000 | አ/አ |
| 173 | አቶ ደስታ መጋቢያው ሃይሉ | 84 | 84,000 | - | አ/አ |
| 174 | አቶ ገነነው አበባው ለምለም | 84 | 84,000 | - | አ/አ |
| 175 | ወ/ሮ ንግስት ደመቀ ጥሩነህ | 84 | 84,000 | - | አ/አ |
| 176 | ወ/ሪት ታደለች ፀጋዬ ገብሩ | 134 | 134,000 | - | አ/አ |
| 177 | ወ/ሮ ቆንጂት ማሞ ወ/ጻድቅ | 150 | 150,000 | - | አ/አ |
| 178 | አቶ አለሙ ታደሰ አዳ | 97 | 97,000 | - | አዳማ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 179 | ወ/ሪት ተዋበች ጥላሁን በቀለ | 150 | 150,000 | - | አ/አ |
| 180 | ወ/ሮ የሺ ገ/ሊባኖስ ተስፋሁነኝ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 181 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ታደሰ አለሙ | 150 | 150,000 | - | አ/አ |
| 182 | ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ አስፋው | 120 | 120,000 | - | አ/አ |
| 183 | ወ/ሮ ወይንሸት ታምራት ደጀኔ | 150 | 150,000 | - | አ/አ |
| 184 | ወ/ሪት ፋና ገ/ህይወት አሰማኸኝ | 168 | 168,000 | - | አ/አ |
| 185 | ወ/ሪት ሰላማዊት ተፈራ ሃ/ሚካኤል | 84 | 62,000 | 22,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 186 | ወ/ሮ ኢትዮጵያ አክሊሉ በሃይሉ | 84 | 61,000 | 23,000 | አ/አ |
| 187 | አቶ ኪዳኔ ወልዳይ አምባዬ | 84 | 84,000 | - | አ/አ |
| 188 | ወ/ሪት ፃድቃን ንጉሴ ምክሩ | 200 | 200,000 | - | አ/አ |
| 189 | አቶ አድማሱ ታደሰ ኃይሉ | 136 | 136,000 | - | ደሴ |
| 190 | አቶ ባንቲ ብሬ ዘለቀ | 118 | 118,000 | - | አ/አ |
| 191 | አቶ እስቲፋኖስ እምሩ እካሎ | 139 | 139,000 | - | አ/አ |
| 192 | አቶ ሙሉጌታ አሰበ ለገሰ | 76 | 61,000 | 15,000 | አ/አ |
| 193 | አቶ ልንገርህ ይታይህ ካሳ | 70 | 47,000 | 23,000 | አ/አ |
| 194 | ወ/ሪት ኤደን ተገኘ አየለ | 100 | 100,000 | - | ድሬዳዋ |
| 195 | አቶ ሂሳቅ ከበደ አብዳ | 70 | 68,000 | 2,000 | አ/አ |
| 196 | ወ/ሪት ሸዋዬ ቡልቡላ ኢንሶ | 118 | 118,000 | - | አ/አ |
| 197 | ወ/ሮ ባንቺ ወሰኑ ዘውዴ | 112 | 112,000 | - | አ/አ |
| 198 | ወ/ሮ አባይነሽ ግዛው ሃ/ማርያም | 98 | 98,000 | - | አ/አ |
| 199 | ወ/ሮ ወይንሸት ስለሺ ይፍሩ | 68 | 68,000 | - | አዳማ |
| 200 | ወ/ሮ እናትሁን ጀምበሬ ይገዙ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 201 | አቶ ዉብሸት በቀለ ካብትይመር | 68 | 59,000 | 9,000 | አ/አ |
| 202 | አቶ ቦጋለ አበራ ደንጋዴ | 68 | 59,000 | 9,000 | አ/አ |
| 203 | ወ/ሮ ክንደሃፍቴ መብርሃቱ ፈትሌ | 68 | 50,000 | 18,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 204 | አቶ መልካሙ ገ/ህይወት ደስታ | 68 | 50,000 | 18,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 205 | አቶ በትረ ሰይፈ ሃ/ሚካኤል | 260 | 260,000 | - | አ/አ |
| 206 | አቶ ብሩክ ቶሎሳ ኮለኒስ | 60 | 60,000 | - | አ/አ |
| 207 | ወ/ሪት ሰላም ቶማስ ደስአለኝ | 110 | 110,000 | - | አ/አ |
| 208 | ወ/ሪት የሹምነሽ ሞላ ተሰማ | 80 | 80,000 | - | አ/አ |
| 209 | አቶ ታከለ ይልማ ገ/ሚካኤል | 60 | 60,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 210 | ወ/ሪት ሃና ተገኘ አዳነ | 70 | 70,000 | - | አ/አ |
| 211 | ወ/ሪት ቅድስት ደምሰው ሞልቶት | 70 | 70,000 | - | አ/አ |
| 212 | አቶ ግሩም ወርቅነህ አበበ | 94 | 94,000 | - | አ/አ |
| 213 | አቶ አመንቲ ቶሎሳ ወልደ | 70 | 70,000 | - | አ/አ |
| 214 | ወ/ሮ የወርቅውሃ አላምነው ወልዴ | 52 | 36,000 | 16,000 | ባህርዳር |
| 215 | ወ/ሪት ለተብርሃን ገ/ህይወት ገ/መድን | 52 | 38,000 | 14,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 216 | አቶ ሰለሞን ከበደ ታረቀኝ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 217 | ወ/ሪት አክሊል ደረጀ ታመነ | 190 | 190,000 | - | አ/አ |
| 218 | ወ/ሪት ረድኤት ለማ ወ/ጊዮርጊስ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 219 | ወ/ሮ አመለወርቅ አለባቸው ውዴ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 220 | ወ/ሪት ሳባ ሃይሉ ተሾመ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 221 | ወ/ሮ እመቤት ሃጎስ ኃ/ስላሴ | 200 | 200,000 | - | አዋሳ |
| 222 | ወ/ሮ ምናሉ ተስፋዬ አያሌው | 180 | 180,000 | - | አዋሳ |
| 223 | ወ/ሮ ወይንሸት ገነነው በቀለ | 64 | 64,000 | - | አ/አ |
| 224 | አቶ ኤዶሚያስ ግርማ ሞላ | 65 | 65,000 | - | አ/አ |
| 225 | አቶ ጌታነህ አሰፋ መኮነን | 50 | 50,000 | - | አ/አ |
| 226 | ወ/ሪት ጽጌረዳ ብርቁ አካል | 50 | 47,000 | 3,000 | አ/አ |
| 227 | አቶ ዘነበ ስዩም ረዳ | 50 | 36,000 | 14,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 228 | ወ/ሮ መልሽው ምትኩ ጎበው | 46 | 30,000 | 16,000 | ባህርዳር |
| 229 | አቶ ሚኒሊክ ደሳለኝ ተክሌ | 56 | 56,000 | - | አ/አ |
| 230 | አቶ አብርሃም ወርቁ ለገሰ | 60 | 60,000 | - | አ/አ |
| 231 | ወ/ሮ ማርታ አሊ አብዱልቃድር | 57 | 57,000 | - | አ/አ |
| 232 | አቶ ይልቃል መንገሻ ዘለቀ | 60 | 60,000 | - | አ/አ |
| 233 | አቶ ይልማ አለሙ ታደሰ | 182 | 182,000 | - | አ/አ |
| 234 | ወ/ሮ አልማዝ ድፋባቸው ተፈራ | 91 | 91,000 | - | አ/አ |
| 235 | አቶ ዘመድኩን አየለ ተሰማ | 42 | 42,000 | - | አ/አ |
| 236 | አቶ አለሙ አድኖ ገብሬ | 51 | 51,000 | - | አ/አ |
| 237 | ወ/ሪት መቅደስ ካሳሁን ደምሴ | 48 | 48,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 238 | አቶ ልክነው አክማች ንጉሴ | 42 | 32,000 | 10,000 | አ/አ |
| 239 | አቶ ተራማጅ አስገልጠው ወልደየስ | 40 | 40,000 | - | አ/አ |
| 240 | ወ/ሪት ዮዲት ተፈራ ረጋሳ | 70 | 70,000 | - | አ/አ |
| 241 | ወ/ሪት ገነት ፍቃዱ ጬምዴሣ | 100 | 100,000 | - | አ/አ |
| 242 | አቶ መሃሪ አብርሃም ሰይፉ | 90 | 90,000 | - | አዋሣ |
| 243 | ወ/ሮ ፅጌ ገ/እየሱስ ወልደ ገሪማ | 99 | 99,000 | - | አ/አ |
| 244 | ወ/ሪት ለምለም ታምሩ ገ/ማሪያም | 40 | 40,000 | - | አ/አ |
| 245 | ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ መንግስቱ | 60 | 60,000 | - | አ/አ |
| 246 | አቶ ተስፋዬ ባሴ አማረ | 67 | 67,000 | - | አ/አ |
| 247 | አቶ ይርጋሸዋ ነጋሽ አማረ | 65 | 65,000 | - | አ/አ |
| 248 | ወ/ሪት ትግስት አለሙ ሹምዬ | 40 | 37,000 | 3,000 | አ/አ |
| 249 | አቶ ታዬ ቀጅሉ ዋቆ | 40 | 35,000 | 5,000 | አ/አ |
| 250 | አቶ ዮናስ ተካ ሹኩር | 40 | 35,000 | 5,000 | አ/አ |
| 251 | አቶ ፀጋዬ ገ/መድህን ንጉስ | 40 | 29,000 | 11,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 252 | አቶ ወልዱ ደባይ መሸሻ | 40 | 29,000 | 11,000 | ትግራይ/ መቐለ |
| 253 | ወ/ሪት ሱመያ የሱፍ አብዱላሂ | 71 | 71,000 | - | አ/አ |
| 254 | ወ/ሪት አረጋሽ ደጀኔ ሙላቱ | 60 | 60,000 | - | አማራ/ ማጀቴ |
| 255 | አቶ ኤርሚያስ ውዴ ተስፋው | 36 | 26,000 | 10,000 | አ/አ |
| 256 | አቶ ሺመልስ ኑርጋ ወ/ጊዮርጊስ | 76 | 76,000 | - | አ/አ |
| 257 | ወ/ሪት ብርሀኔ ደረጀ ሊበን | 36 | 36,000 | - | አ/አ |
| 258 | ወ/ሪት ሰላማዊት በሪሁን አፅብሃ | 36 | 36,000 | - | አ/አ |
| 259 | ወ/ሪት አስናቀች አክታ ራምሻ | 36 | 36,000 | - | አ/አ |
| 260 | አቶ ወንድወሰን ፀጋዬ ተሰማ | 36 | 34,000 | 2,000 | አ/አ |
| 261 | ወ/ሪት ሀና ደቁሴ ገ/ማርያም | 36 | 36,000 | - | አ/አ |
| 262 | ወ/ሪትኤልሳቤት ተፈራ የ/ብርሃን | 36 | 28,000 | 8,000 | አ/አ |
| 263 | አቶ ቴዎድሮስ ግርማ ገረሳ | 30 | 30,000 | - | አ/አ |
| 264 | ወ/ሪት ተናኜ እሸቱ ወ/ሚካኤል | 59 | 59,000 | - | አ/አ |
| 265 | አቶ እስራኤል አበራ ኪዳኔ | 46 | 46,000 | - | አ/አ |
| 266 | ወ/ሪት ሜሮን አሸኔ ገረመው | 75 | 75,000 | - | አ/አ |
| 267 | ወ/ሪት አበበች ደስታ ደጀኔ | 32 | 32,000 | - | አ/አ |
| 268 | ወ/ሪት እመቤት አዳሙ መርጋ | 35 | 35,000 | - | አ/አ |
| 269 | ወ/ሪት ገነት ዘማ አባተ | 110 | 110,000 | - | አዋሳ |
| 270 | አቶ በለጠ ስሜ ሳህሌ | 30 | 23,000 | 7,000 | አ/አ |
| 271 | ወ/ሪት ኤደን ከበደ በየነ | 28 | 21,000 | 7,000 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 272 | አቶ አብዩ አለኸኝ ሲሳይ | 70 | 70,000 | - | አ/አ |
| 273 | አቶ መስፍን ጉታ ሽርሙ | 53 | 53,000 | - | አ/አ |
| 274 | ወ/ሪት ነፃነት አብርሃም ሰማ | 37 | 37,000 | - | አ/አ |
| 275 | ወ/ሪት ደሱ ዋክታሱ ገላና | 26 | 18,000 | 8,000 | አ/አ |
| 276 | አቶ ኤርሚያስ እሸቱ አወቀ | 34 | 34,000 | - | ድሬዳዋ |
| 277 | ወ/ሮ ገነት ግርማ ወርዶፋ | 35 | 35,000 | - | አ/አ |
| 278 | አቶ ክብሮም አብርሃ ካሕሳይ | 20 | 20,000 | - | ትግራይ/ መቐለ |
| 279 | ወ/ሮ ዘበኛሽ አስፋው ዓለማየሁ | 70 | 70,000 | - | ጎንደር |
| 280 | አቶ ከድር አብደላ ጀማል | 20 | 20,000 | - | ጎንደር |
| 281 | ወ/ሪት ኤደን ሚካኤል ደበሳይ | 20 | 20,000 | - | ጎንደር |
| 282 | አቶ ትልቅሰው አስፋው ሙሃበው | 20 | 20,000 | - | ጎንደር |
| 283 | አቶ ተክሉ ስዩም ተ/ጊዮርጊስ | 55 | 55,000 | - | አ/አ |
| 284 | ወ/ሮ ሰሞሃር ታምሩ ያደቴ | 30 | 30,000 | - | አ/አ |
| 285 | ወ/ሪት ቅድስት ሃ/ሚካኤል ሐብቴ | 28 | 28,000 | - | አ/አ |
| 286 | ወ/ሪት ገነት አሰፋ ገበየሁ | 39 | 39,000 | - | አ/አ |
| 287 | ወ/ሪት ሊያ ፈይሳ መኮነን | 32 | 32,000 | - | ሱሉልታ |
| 288 | ወ/ሪት ምስራቅ ድራራ ሀጎስ | 30 | 30,000 | - | አ/አ |
| 289 | ወ/ሪት አስቴር ዘውዱ ሃወዝ | 22 | 22,000 | - | አ/አ |
| 290 | አቶ ፍቃዱ መራ ወ/ጊወርጊስ | 24 | 24,000 | - | አ/አ |
| 291 | ወ/ሪት ትግስት ታደሰ ተሰማ | 20 | 20,000 | - | አ/አ |
| 292 | ወ/ሪት ዙፋን አለማየሁ ሰንበታ | 30 | 30,000 | - | አ/አ |
| 293 | ወ/ሮ መንበረ ተስፋዬ ፍቃዱ | 29 | 29,000 | - | አ/አ |
| 294 | አቶ በላይነህ አብተው ታረቀ | 18 | 17,000 | 1,000 | ደሴ |
| 295 | ወ/ሪት እየሩሳሌም ሀይሉ ሞገስ | 16 | 16,000 | - | አ/አ |
| 296 | አቶ ተስፋሁን ዘሪሁን በቀለ | 32 | 32,000 | - | አ/አ |
| 297 | ወ/ሮ ማህሌት ግርማ ተ/ማሪያም | 72 | 72,000 | - | አዳማ |
| 298 | አቶ ኢብራሂም አህመድ መሀመድ | 14 | 12,000 | 2,000 | አ/አ |
| 299 | አቶ አቤነዘር ደረሰ መንግስት | 22 | 22,000 | - | አ/አ |
| 300 | አቶ ሲሳይ ደጀኔ ሀብቴ | 50 | 50,000 | - | አ/አ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 301 | አቶ አሸናፊ ከበደ ጨንቆ | 50 | 50,000 | - | |
| 302 | ወ/ሪት ዜና ፍሰሃ አበራ | 10 | 10,000 | - | አ/አ |
| 303 | ወ/ሪት ብሩክታዊት ዮሃንስ ሳህሌ | 30 | 30,000 | - | አ/አ |
| 304 | ወ/ሮ ትዝታ መለሰ ደበሌ | 11 | 11,000 | - | አ/አ |
| 305 | ወ/ሪት እጅጋየሁ ጥላሁን ገ/ፃዲቅ | 21 | 21,000 | - | አ/አ |
| 306 | ወ/ሪት እመቤት አባተ ጋሻው | 26 | 26,000 | - | አ/አ |
| 307 | ወ/ሮ ሙሉነሽ ፍጹም ገብረ ተክሌ | 30 | 30,000 | - | ደሴ |
| 308 | አቶ ምስጋን አደገ ጀመረ | 50 | 50,000 | - | አ/አ |
| **ድምር** | | **87,689** | **76,755,000** | **10,934,000** | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **357,897** | **275,946,000** | **81,951,000** | |

## አንቀፅ 4. የማህበሩ የንግድ አላማና የሥራ ዘርፍ

ማህበሩ የሚከተለው ዓላማና የሥራ ዘርፍ ይሠራል፡-

1. በሕይወት የመድን ሥራ፣ በግዴታ በየጊዜው የሚከፈል ገንዘብ የመክፈል ሥራ፣ በጡረታ የመድን ሥራ፣ በቋሚ የጤና መድን ሥራ፣ በሰው አካል በሚደርስ አደጋ የመድን ሥራ፣ በሕመም የመድን ሥራ፣ በጠቅላላ የመድን ሥራ፣ እና በጠለፋ የመድን ሥራ በመሰማራት ተገቢውን አገልግሎት መስጠት፣
2. መያዣን ጨምሮ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ማናቸውም የንግድ ሥራ፣ ማናቸውም ዓይነት ዋስትና የሚመለከት ሥራ፣ አክሲዮኖችን መሸጥን ሆነ መለወጥን ጨምሮ አክሲዮኖችን የሚመለከት ማናቸውም የንግድ ሥራ እና ማዋዕለ ንዋይን በማደበር ሆነ በማቀጣት በንግድ ሥራ ላይ ማዋልን የሚመለከት ማናቸውንም የንግድ ሥራ መስራት፣
3. ለቢሮ አገልግሎቶችና ለተያያዥ ጉዳዮች የሚጠቀምባቸውን ሕንፃዎች ማስገንባትና የተገነቡትን ሕንፃዎች በከፊል ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የማከራየትና የመጠቀም ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡
4. ከዚህ በላይ የተገለፀውን የንግድ ዓላማውን ለመተግበር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያግዝ ማናቸውንም ሥራ መስራት፣ ነው፡፡

## አንቀፅ 5. ዋና ገንዘብ

1. የማኀበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ እኩል በሆኑና በያንዳንዱ አክሲዮን ላይ ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) የመነሻ ዋጋ የተፃፈባቸው ሆኖ ሁሉም አክሲዮኖች ተራና የተመዘገቡ ሆነው 357,897.00 (ሶስት መቶ አምሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት) የተፈረሙ አክሲዮኖች፣ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ብር 357,897,000.00 (ሶስት መቶ አምሳ ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ ብር) ነው።
2. ከአክስዮኖች ዋጋ ውስጥ ብር 275,946,000 (ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ብር) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሎ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ንግድ ባንኮች፣ የተለያዩ ቅርንጫፎች በማኀበሩ ስም በተከፈተ ሂሳብ ገቢ ሆኖአል።
3. የአክስዮን መዋጮዎች በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ነው። በዓይነት ተደረ መዋጮ የለም።

## አንቀፅ 6. ስለትርፍ አከፋፈል

1. የማኀበሩ የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው ባሉአቸው አክሲዮኖች መጠን ይሆናል።
2. የተጣራ ትርፍ መቼና በምን ሁኔታ እንደሚከፋፈል የሚወስነው የማኀበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።(ስለ ባለ አክሲዮኖች ጉባኤዎች ዝርዝሩ በክፍል ሁለት ንዑስ ክፍል II ቀርቧል።)

## አንቀፅ 7. የሥራ አመራር፡- የዳሬክቶሮች ቦርድ

1. ማኀበሩ ብዛታቸው ዘጠኝ በሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይተዳደራል።
2. የማህበሩ ዳይሬክቶሮች ቦርድ አባላት በማህበሩ ባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ መደበኛ ጉባኤ ይሾማሉ። የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሦስት(3) ዓመት ነው። ሆኖም የቦርድ አባል እንደገና ሊመረጥ ይችላል።
3. የማኀበሩ አመራርን በሚመለከት ዳይሬክተሮቹ የማይነጣጠል የጋራ ኀላፊነት አለባቸው።
4. እያንዳንዱ ዳይሬክተር በማናቸውም የዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ አንድ ድምፅ ይኖረዋል። የሃሳብ ልዩነት በሚከሰትበት ጊዜ አብዛኞቹ አስተዳደር ቦርዱ አባላት የደገፉት ሃሣብ ውሳኔ ይሆናል።

5. የዳይሬክተሮች ቦርዱ በፈቀደለት መጠን ካልሆነ በቀር ማንኛውም ዳይሬክተር በተናጠል በማኅበሩ ላይ ኀላፊነት የሚያስከትል እርምጃ መውሰድ አይችልም።
6. የዳይሬክተሮች ቦርዱ በ2013 ዓ.ም በወጣው የንግድ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 337(1) እና 340 እንዲሁም የመድን ሥራን ለመደንገግ  በወጣው አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀፅ 15 መሠረት የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ፀሐፊ ይሾማል።
7. በሕግ የተወሰነው ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዳይሬክተሮች ቦርዱ፣

   ሀ/ ማናቸውም የማኅበሩ ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዢን፣ ሽያጭ፣ ኪራይን ወይም መያዣነት የመፍቀድ፣ እና

   ለ/ በሕግ በግልፅ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ የባለአክሲዮኖች የማህበሩን ሂሳቦች መፃሕፍት እና ሌሎች ሰነዶች በምን ደንቦችና ገደቦች የመመርመር መብት እንደሚኖራቸው፣ የመመርመር መብቱ ካላቸውም እስከምን ድረስ፣ መቼ እና የት ቦታ መሆኑን የመወሰን፣ ተጨማሪ ስልጣን ይኖረዋል። (ዝርዝሩ በክፍል ሁለት ንዑስ ክፍል III ተመልክቷል።)

## **አንቀፅ 8. ተቆጣጣሪዎች**

1. የማህበሩ ተቆጣጣሪዎችና ረዳት ተቆጣጣሪዎች በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ።
2. የማህበሩ ተቆጣጣሪዎች እና ረዳት ተቆጣጣሪዎች በሕግ፣ በዚህ መመሥረቻ ፅሁፍ እና በባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች ውሳኔዎች መሠረት በሥራቸው ሙሉ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።(ዝርዝሩ በክፍል ሁለት ንዑስ ክፍል Vተመልክቷል።)

## **አንቀፅ 9. የማህበሩ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶች**

የማኅበሩ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት በየዓመቱ እያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት ከተዘጋበት ቀን (እ.ኤ.አ ከጁን 30 ቀን) ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ለጠቅላላ ጉባኤው ይቀርባል። (ዝርዝሩን በክፍል ሁለት ንዑስ ክፍል VII አንቀጽ 30 ተመልክቷል።)

## **አንቀፅ 10. ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ**

በሕግና በማኅበሩ መመስረቻ ፁሑፍ መሠረት የማኅበርተኞቹ ማህበሩን የማፍረስ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

## ክፍል ሁለት፡- ዝርዝር ድንጋጌዎች

## ንዑስ ክፍልI- አክስዮኖች፡፡

## አንቀጽ 1- አክስዮኖችን የማግኘት መብት፡፡

1. የፈረመውን አክሲዮን ዋጋ በሙሉ የከፈለ ማንኛውም ባለአክሲዮን መዋጮውን የሚወክሉ የአክሲዮኖች ድርሻ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. እያንዳንዱ አክሲዮን በማኀበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ተፈርሞ የማሕበሩ ማኅተም ይታተምበታል፡፡
3. በእያንዳንዱ አክሲዮን ላይ፣

   ሀ) የማኅበሩ ስም፣ ዋና መሥሪያ ቤት እና የሚቆይበት ጊዜ፣

   ለ) የማኅበሩ ዋና ገንዘብ እና የአክስዮን ዋጋ (ፖር ቫልዩ)

   ሐ) የመመሥረቻው ጽሑፍ የተፈረመበት ቀን፣ ማኀበሩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበት ቀን እና የተመዘገበበት ቦታ፣

   መ) የአክሲዮን መለያ ተራ ቁጥር እና ተራ አክሲዮን መሆኑ፣

   ሠ) የአክሲዮኑ ዋጋ (ፖር ቫልዩ) በሙሉ መከፈሉ፣ እና

   ረ) አክሲዮኑ በባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገበ መሆኑ መግለጽ አለበት፡፡

## አንቀጽ 2- የጠፉ የአክሲዮን ሰርተፍኬቶችን ስለመተካት፡፡

1. የአክሲዮኖቹ ሰርተፍኬት የጠፉበት ባለአክሲዮን ሰርተፍኬቶቹ ለመጥፋታቸው ለሚመለከተው መንግስታዊ አካላት በአግባቡ የተሰጠ ቃለ መሃላ ወይም ማናቸውም ሌላ አስተማማኝ ማስረጃ ሲያቀርብ በጠፉበት ሰርተፍኬቶች ምትክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አዲስ አክሲዮኖች ይሰጠዋል፡፡
2. የዳይሬክተሮች ቦርዱ የጠፉትን ሰርተፍኬቶች የሚተኩ አዲስ ሰርተፍኬቶች ከመስጠቱ በፊት አስፈላጊ ብሎ በሚወስነው መንገድ ባለ አክሲዮኑ ሰርተፍኬቶች መጥፋት ለሕብረተሰቡ እንዲያሳውቅና ጠፋ በሚባሉት ሰርተፍኬቶች ምክንያት በማኀበሩ ላይ ሊቀርብ ለሚችል የክፍያ ሆነ የማናቸውም ሌላ ጥያቄ የሚውል የተወሰነ ገንዘብ እንዲያስይዝ ለማድረግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 3-አክሲዮኖችን ስለማስተላለፍ፡፡

1. አክሲዮኖችን ማስተላለፍ በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚቀመጠው የአክሲዮኖቹ መዝገብ መተላለፋቸውን በማስመዝገብ ብቻ ይሆናል፡፡
2. የሟች ማኅበርተኛ አክሲዮን በሕግ ወይም በሟች ኑዛዜ መሠረት ለሚገባቸው ወራሾች ይተላለፋሉ፡፡

## አንቀጽ 4- ማስተላለፍን ስለማገድ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ከማናቸውም የባለ አክሲዮኖች ስብሰባ በፊት ከአምስት (5) ቀኖች ለማይበልጥ ጊዜ የአክሲዮኖች መተላለፍን ሊያግድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 5- የአክሲዮኖች መዝገብ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት የሚቀመጥ በሕግ፣ በማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ፣ አግባብነት ባለው መመሪያ እና በማናቸውም የማሕበርተኞች ጠቅላላ ጉባኤ በሚተላለፍ ውሳኔ መሠረት መመዝገብ ያለበት ማናቸውም ነገር የሚመዘገብበት መዝገብ ያኖራል፡፡
2. የዳይሬክተሮች ቦርዱ ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ መሠረት በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚያኖረው መዝገብ የተሳሳተ ምዝገባ መኖሩ በተገለጸለት ወይም ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአሥራ አምስት (15) ቀኖች ውስጥ ስህተቱን ያርማል፡፡

## አንቀጽ 6- የባለአክሲዮን መብት፡፡

1. በማህበሩ የአክሲዮኖች መዝገብ በባለአክሲዮንነት የተመዘገበ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን፣
   ሀ) በማናቸውም የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ራሱ ወይም በአንደራሴው አማካይነት በመገኘት በጉባኤው የመሳተፍ፣
   ለ) በማናቸውም የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ራሱ ወይም በአንደራሴው አማካይነት በመገኘት ባሉት የአክሲዮኖች መጠን ድምጽ የመስጠት፣
   ሐ) የማኅበሩን የንብረት ዝርዝር መግለጫ፣ የሂሳብ ሚዛን፣ የዳይሬክተሮች ዘገባ እና የተቆጣጣሪዎች ዘገባ በመመርመር በራሱ ወጪ ቅጂአቸውን የመውሰድ፣
   መ) የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ከፍ ለማድረግ ከሚወጡት አክሲዮኖች ባሉት አክሲዮኖች መጠን ድርሻውን የመጠየቅ፣ እና
   ሠ) በሕግ፣ በማሕበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ እና አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሠረት በሌሎች የባለአክሲዮን መብቶች ሁሉ የመጠቀም፣ መብት ይኖረዋል፡፡

## ንዑስ ክፍል II-የባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች፡፡
## አንቀጽ 7- የመጨረሻ የሥልጣን አካል፡፡

1. የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ማኅበሩን በሚመለከት በማናቸውም ጉዳይ የማኅበሩ የመጨረሻ የበላይ ባለሥልጣን ነው፡፡
2. ሆኖም ይህ የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ሥልጣን የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤን ወይም የአስተዳደር ቦርዱን የማይመለከቱ የባለአክሲዮን መብቶችን በሚመለከትም የጉባኤው ወይም የአስተዳደር ቦርዱ ሥልጣን እንዳለው ተደርጎ ሊታይ አይችልም፡፡
3. የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በሕግ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በተጨማሪ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተለው ኃላፊነት አለው፡፡

3.1. የአክሲዮን ማህበሩን አጠቃላይ ፖሊሲ መመሪያ ያወጣል፣ የማህበሩን የዓመቱን በጀት እና የሥራ ፕሮግራም ያፀድቃል፡፡

3.2. በሕጉ መሠረት የማህበሩን ካፒታል ይቀንሳል ወይም ይጨምራል፣ ስለማህበሩ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት ከሌላ ኢንሹራንስ ወይም ሌላ ማህበር ጋር ስለመዋሃድ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

3.3. በማህበሩ የትርፍ ድርሻዎች አከፋፈል ይወስናል፡፡

3.4. ቋሚ እና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥልጣናቸውንና ተግባራቸውን ይወስናል፣

3.5. የቦርዱ አባላት ለሆኑት የማህበሩ ባለሥልጣናት ለሚያበረክቱት አገልግሎት የሚገባቸውን ክፍያ ይወስናል፣

## አንቀጽ 8- ጉባኤዎችን ስለመጥራት፡፡

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤዎች እንዲደረጉ የማኅበሩ አስተዳዳሪዎች፣ ኦዲተሮች ወይም ሂሳብ አጣሪዎች ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ጥሪ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡
2. በማህበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አንድ አሥረኛውን የሚወክሉ አክሲዮኖች ያሉአቸው ባለአክሲዮኖች አቤቱታ ካቀረቡለት አቤቱታውን ለማየት ሥልጣን ያለው የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ የሚያስችል ፍርድ ቤት የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ የሚጠራ የፍርድ ቤት ሹም ሊሰይም ይችላል፡፡

3. የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እያንዳንዱ የማኅበሩ የሂሳብ ዓመት ካለቀ በኋላ በሚኖሩት በመጀመሪያዎች ስድስት (6) ወሮች ውስጥ የማኅበሩ ባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ ተገቢውን የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡
4. የማሕበሩን የመመሥረቻ ጽሑፍ ማሻሻል፣ የማሕበሩን ዜግነት መለወጥ ወይም ባለአክሲዮኖች ለማሕበሩ ያደረጉትን መዋጮ እንዲጨምር ማድረግ የሚቻለው የማሕበሩ ባለአክሲዮኖች በሚያደርጉት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ብቻ ይሆናል፡፡
5. የማሕበሩ ባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች ሁሉ የሚካሄዱት የዳይሬክተሮች ቦርዱ በሚወስነው ቦታ ይሆናል፡፡
6. የአክስዮኖች መዝገብ ኃላፊ የሆነው የማሕበሩ ባለስልጣን ማናቸውም የማሕበሩ ባለአክሲዮኖች ጉባኤ ከመደረጉ ከአምስት (5) ቀኖች በፊት በባለአክሲዮኖች የስም ተራ ፊደል መሠረት ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው የባለአክሲዮኖች ስም በሙሉ አድራሻቸውና በእያንዳንዳቸው ስም የተመዘገቡትን የአክሲዮኖች ብዛት ጭምር የሚያሳይ የተሟላ የስም ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡
7. ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት የተዘጋጀ የባለ አክሲዮኖች በሙሉ የስም ዝርዝር በማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት እና በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች የባለ አክሲዮኖች ጉባኤ ከመደረጉ በፊት ቢያንስ ለአምስት (5) ቀኖች ማናቸውም ባለአክሲዮን ሊያየው በሚችልበት ሁኔታ ይቆያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በስብሰባው ራሱ ወይም በአንደራሴው አማካይነት የሚሳተፍ ማንኛውም ባለአክሲዮን ሲፈልግ እንዲያየው ለማድረግ ይቻል ዘንድ ጉባኤው በሚደረግበት ጊዜም ጉባኤው በሚደረግበት ቦታ የስም ዝርዝሩ መኖር አለበት፡፡
8. ከዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ የባአክሲዮኖች ጉባኤ በስተቀር በማናቸውም የማሕበሩ ባለ አክሲዮኖች ጉባኤ መወያየት እና ድምፅ መስጠት የሚቻለው ጉባኤው በተጠራበት ጉዳይ ብቻ ይሆናል፡፡
9. ማናቸውም ጉባኤ እንዲደረግ ለባለአክሲዮኖቹ ጥሪ ቢተላለፍ ከጉባኤው በፊት ሊሰጣቸው የሚገባ ጊዜ በ2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 370 እንደተደነገገው ጉባኤው ከሚደረግበት ቀን ሃያ አራት ቀናት በፊት ይሆናል፡፡

## <u>**አንቀጽ 9- የጉባኤዎች አመራር፡፡**</u>

1. ማናቸውም ጠቅላላ ጉባኤ በዳይሬክተሮች ቦርዱ ሊቀመንበር ወይም፣ ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ጊዜ፣ በዳይሬክተሮች ቦርዱ ምክትል ሊቀመንበር ሰብሳቢነት ይካሄዳል፡፡
2. በእያንዳንዱ ጉባኤ ራሳቸው ወይም በእንደራሴዎቻቸው አማካይነት የተገኙ ባለ አክሲዮኖች እና የድምጽ ብዛት በዝርዝር የሚያሳይ የባለአክሲዮኖች እና የድምጽ ብዛት በዝርዝር የሚያሳይ የባለአክስዮኖች መገኘትና መቅረት መቆጣጠሪያ ሰነድ እየተዘጋጀ በሰነድነት ይቀመጣል፡፡
3. ለእያንዳንዱ ጉባኤ በድምጽ ተቆጣጣሪነት የሚያገልግሉ ሁለት ባለአክሲዮኖች ይመረጣሉ፡፡
4. ጉባኤዎችን በሚመለከት አስፈላጊውን ምልዓተ ጉባኤ እና ድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት በ2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 እንደተደነገገው ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል III -የሥራ አመራር

## አንቀጽ 10- የዳሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

በሕግ፣በመመሥረቻ ፅሁፍና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች/ውሳኔዎች ከተሰጠው ሥልጣንንና ተግባር በተጨማሪ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1. የማህበሩን የውስጥ ደንብ ያፀድቃል፣
2. የማህበሩን ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የቦርድ ፀሐፊ ይሾማል፣ ያሰናብታል፣
3. የቦርዱ አባላት ላልሆኑት የማህበሩ ባለሥልጣናት የሚገባቸውን ክፍያ ይወስናል፣
4. በረቂቅ መልክ የቀረበውን የዓመቱን በጀት እና የሥራ ፕሮግራም ያጣራል፣
5. የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን መክፈት ወይም መዘጋት ያፀድቃል፣
6. የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣
7. የማህበሩን የሥራ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ እንዲያስችለው ገንዘብ ይበደራል፣
8. ለማህበሩ ዋና ሥ/አስኪያጅ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑትን ኃላፊዎች ቅጥር፣ የሥራ ድርሻ እና ስንብት ያፀድቃል፣
9. የማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በሙሉ በሕጉ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣
10. በማህበሩ ተገቢ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት መያዛቸውን ያረጋግጣል፣
11. ቦርዱ ዋናውን ሥ/አስኪያጅ እና የማህበሩን ሠራተኞች የመወከል ሥልጣን አለው፣

## አንቀጽ 11
## የዋስትና አክሲዮኖች

እያንዳንዱ የማህበሩ ዳይሬክተር በአመራር ላይ በሚቆይበት ጊዜ በማህበሩ ቢያንስ አሥር /10/ አክሲዮኖች ይኖሩታል።

## አንቀጽ 12
## ክፍት ቦታዎች

1. አባላቱ የተመረጡበት የሦስት ዓመት የአገልግሎት ዘመን ከማለቁ በፊት የቦርዱ አባላት ቁጥር ከተወሰነው በታች ሆኖ ከተገኘ በየዓመቱ የሚደረገው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምርጫውን የማጽደቅ ወይም የመሻር ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቀሪዎቹ የማኅበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ከማህበሩ ባለአክሲዮኖች መካከል በመምረጥ በጎደለው አባል ምትክ ይሾማሉ።

2. ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ቀሪዎቹ የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ያደረጉትን ምርጫ የባለአክሲዮኖቹ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከሻረው ክፍቱን ቦታ የሚሸፍን ሌላ ባለአክሲዮን ይሾማል።

3. ለማህበሩ ከተወሰኑት የዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት ቦታዎች ከግማሽ በላይ ክፍት ሆነው ከተገኙ ግን ቀሪው የማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ አባል በቦታዎቹ ሌሎች አባላት እንዲመደቡለት የማህበሩ ማህበርተኞች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል።

## አንቀጽ 13
## ስብሰባዎች

1. ማናቸውም የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባ የሚያደርገው በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ይሆናል፡፡
2. በማናቸውም የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባ ከአባላቱ አብዛኞቹ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት መደበኛ ስብሰባዎች እና ልዩ ስብሰባዎች ይኖሩአቸዋል፡፡
4. የቦርድ አባላት በሚያደርጉት የመጀመሪያ ስብሰባዎች የስብሰባውን ሊቀመንበር በመምረጥ ማህበሩን የማስተዳደር ተግባራቸውን መወጣት ያስችላቸው ዘንድ በየወሩ ሊያደርጉአቸው የሚገባ የመደበኛ ስብሰባዎቻቸው ብዛት ይወሰናሉ፡፡
5. የዳሬክተሮች ቦርዱ ሊቀመንበር ሲጠራ ሁኔታዎች እንዲፈቀዱ ወዲያውኑ የቦርዱ ልዩ ስብሰባዎች ይደረጋሉ፡፡
6. የቦርዱ አባላት ስብሰባው እንዲቀየር በሙሉ መፍቀዳቸውን በፊርማቸው በማረጋገጥ በጽሁፍ ከሰጡ እና ይህ ፈቃድ ከየስብሰባቸው ቃለ ጉባኤዎች ተያይዞ እስከተቀመጠ ድረስ በማናቸውም ዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በሚሰጥ ውሳኔ መወሰድ የሚገባው እርምጃ ያለስብሰባው ሊወሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 14
## ክፍያ

1. የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሚያበረክቱት አገልግሎት የተወሰነ ገንዘብ ወይም ደመወዝ ሊከፈላቸው ይችላል፡፡
2. ክፍያው የሚወሰነው በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ ማንኛውንም የዳሬክተሮች ቦርድ አባል ማህበሩን በሌላ ሥራ ከማገልገልና ለዚሁ ለሌላው ሥራውም የሚገባውን ክፍያ ከማግኘት አያግደውም፡፡

# ንዑስ ክፍል IV የማህበሩ ኃላፊዎች እና ሌሎች ሠራተኞች
## አንቀጽ 15
## መሾም

የማህበሩ ኃላፊዎች፣ ማለትም የማህበሩ አስተዳደር ቦርዱ ሊቀመንበር፣ምክትል ሊቀመንበር ፣ፀሐፊ እና የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ፣ በማህበሩ አስተዳደር ቦርድ ይሾማሉ፡፡

## አንቀጽ 16
## ክፍያ

1. የማህበሩ አስተዳደር ቦርድ አባላት ላልሆኑ ለማህበሩ ኃላፊዎች የሚደረግላቸው ክፍያ በማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ ይወሰናል።

2. የማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ አባልነትም ለሚመለከታቸው ለማህበሩ ኃላፊዎች የሚደረግላቸው ክፍያ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል።

## አንቀጽ 17
## የሥራ ኃላፊዎች ተግባራት

1. የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር በሕግ፣ በማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ ከተወሰነው ተግባሩ በተጨማሪ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤዎች የሚያስተላልፏቸውን ውሳኔዎች እና የአስተዳደሩ ቦርድ ውሳኔዎች በሙሉ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

2. ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ወይም፣ በክልከላም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት፣ ሥራውን መሥራት በማይችልበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበሩ የሊቀመንበሩን ተግባራት ሁሉ የማከናወንና የአስተዳደሩ ቦርድ በየጊዜው በሚወስነው መሠረት ተገቢውን የመፈፀም ተግባር ይኖረዋል።

3. ለማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ የተወሰነው ማህበሩን የሚያስተዳድር ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ማናቸውንም ማህበሩን የማስተዳደር ተግባር ለመፈፀም ሙሉ ሥልጣን ያለው የማህበሩ ዋና ኃላፊ ነው።

4. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ (Managing Director) የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

    4.1. የማህበሩን ሥራ ያቀናጃል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
    4.2. ሶስተኛ ወገንን በሚመለከት እና ሲከስም ሆነ ሲከሰስ ማህበሩን ይወክላል፣
    4.3. ቦርዱን በማማከርና በማስፈቀድ በቀጥታ ለእሱ ተጠሪ የሆኑትን የማህበሩ ኃላፊዎችን ይሾማል፣
    4.4. የውስጥ ደንቡ በሚፈቅደውና ቦርዱ ባፀደቀው የደመወዝ ስኬል መሠረት ሌሎች የማህበሩን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያዘውራል፣ ያሰናብታል፣
    4.5. ተገቢ የሆነ የማህበሩ ሂሳብ መዝገብ መያዝ፣ ቦርዱ ሲፈቅድ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ክፍያዎችን ይፈፅማል ወይም ገንዘብ ይቀበላል፣ እንዲሁም ሌሎች የማህበሩን ሥራዎችን ያከናውናል።

4.6. የውስጥ ደንቡን ረቂቁን የዓመት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት፣ የዓመቱን በጀትና የሥራ ፕሮግራሙን በማዘጋጀት ለቦርዱ በማቅረብ ያፀድቃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

4.7. የቦርዱን ውሣኔ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣

4.8. የማህበሩን ወኪሎች ይሾማል፣ ያሰናብታል፣ የሚሰጣቸውን ክፍያ ይወስናል፣

4.9. እንደአስፈላጊነቱ ለማህበሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ውክልና ይሰጣል፣

4.10. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የማህበሩ ቦርድ ሲፈቅድ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን ይከፍታል፣ ይዘጋል፣

4.11. ቦርዱ የሚሰጠውን ሌላ ሥራ ያከናውናል፣

5. የማህበሩ ቦርድ ፀሐፊ ለሚያደርጉት የባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች ሁሉ ለባለአክሲዮኖች መሰጠት ያለባቸውን ማስታወቂያዎች እንዲሰጡ የማስደረግ፣ በማህበሩ ባለአክሲዮኖች በሚደረጉት ጉባኤዎች ሁሉ እና በማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ በሚደረጉት ስብሰባዎች ሁሉ በመገኘት የጉባኤዎቹን እና የስብሰባዎቹን ሂደት የሚያሳዩ ቃለ ጉባኤዎች የማዘጋጀት እና በሕግ፣ በማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ፣ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች እና በማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች በሚተላለፉ ውሳኔዎች መሠረት በጽሁፍ መያዝ ያለበት በመያዝ ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች መላክ የሚገባቸውን የማህበሩን ሰነዶች የመላክ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 18
## ሌሎች ሠራተኞች

1. ዋና ሥራ አስኪያጁ ከማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ጋር በመመካከር በሕግ፣ በማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ፣ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎችና የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች በሚያስተላልፏቸው ውሳኔዎች መሠረት መያዝ ያለባቸውን የማህበሩን ሂሳቦች እና ዘገባዎች የሚይዝ የሂሳብ ሹም ይሾማል፡፡
2. የማህበሩ የሥራ አንቅስቃሴ በሚጠይቀው መጠንም እንደዚሁ፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ ከማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ጋር በመመካከር ሌሎች ሠራተኞች ይቀጥራል፡፡

## ንዑስ ክፍል V ተቆጣጣሪዎች
## አንቀጽ 19
## ሹመት

1. የማህበሩ የሂሳብ ተቆጣጣሪዎች እና ረዳት የሂሳብ ተቆጣጣሪዎች የአገልግሎት ዘመን ሦስት /3/ ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ተቆጣጣሪው እና ረዳት ተቆጣጣሪው እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

2. የተቆጣጣሪዎች እና የረዳት ተቆጣጣሪዎች የአገልግሎት ዘመን ሲያልቅ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተቆጣጣሪዎችን እና ረዳት ተቆጣጣሪዎችን ይሾማል፡፡

3. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በማናቸውም ጊዜ ማንኛውንም ተቆጣጣሪዎች ወይም ረዳት ተቆጣጣሪዎች በበቂ ምክንያት በማሰናበት በምትካቸው ሌሎች ተቆጣጣሪዎች ወይም ረዳት ተቆጣጣሪዎች መሾም ይችላል፡፡

## አንቀጽ 20
## ክፍት ቦታዎች

የተቆጣጣሪዎች ሆነ የረዳት ተቆጣጣሪዎች ቦታ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ወዲያውኑ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት ተቆጣጣሪዎች ወይም ረዳት ተቆጣጣሪዎች በማስሾም በክፍት ቦታው እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 21
## ክፍያ

ለማህበሩ ተቆጣጣሪዎች እና ረዳት ተቆጣጣሪዎች ሊደረግላቸው የሚገባ ክፍያ በማህበሩ ባለ አክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 22
## ተግባራት

በሕጉ መሠረት እንዲያከናውኑአቸው ከሚጠበቁባቸው ተግባራት በተጨማሪ ተቆጣጣሪዎች እና ረዳት ተቆጣጣሪዎች፡-

ሀ/ የማህበሩን የሂሳብ መጻህፍት ትክክለኛነት እና ማህበሩ ከባለእዳዎች ሊከፈል የሚገባ ገንዘብ እንዲከፈለው ለማስደረግ ይችል ዘንድ ያለው የመያዣ መብት ተፈፃሚነት የማረጋገጥ፤

ለ/ የማህበሩ የንብረት ዝርዝር ቆጠራ፣ የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍ እና የኪሳራ ስሌት ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤

ሐ/ የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ዘገባ ማህበሩ በዘገባው ዓመት የነበረው የነበረበትን ሁኔታ በትክክል መግለጹን የማረጋገጥ፣

መ/ የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ተገቢ አለመሆኑን ይገነዘብ ዘንድ ቦርዱ እንዲያውቀው በማድረግ ተገቢ ነው ብለው በሚያምኑበት መጠን ከፊል በሆነ ሁኔታ የማህበሩን ሂሳብ የመመርመር እና የማህበሩን ሂደት ለማሳየት የሚያስችል ማናቸውም ሌላ ምርመራ የማድረግ፣ እና

ሠ/ በማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ እና በማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሠረት የሚመደቡላቸውን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፤ኃላፊነት አላቸው።

## ንዑስ ክፍል VI
## አንቀጽ 23
## የባለአክሲዮኖች ጉባኤ እንዲደረግ የሚያሳስብ ማስታወቂያ

1. ማናቸውም የባለአክሲዮኖች ጉባኤ እንዲደረግ በማሳሰብ ለባለአክሲዮኖች የሚተላለፈው ማስታወቂያ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሪኮማንዲ መላክ አለበት።
2. ሪኮማንዲው ለእያንዳንዱ የማኅበሩ ባለአክሲዮን በሪኮማንዲ የሚላክበት አድራሻም እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ለማህበሩ በሰጠው አድራሻ በኩል ይሆናል።

## አንቀጽ 24
## የአስተዳዳሪዎች ስብሰባ እንዲደረግ የሚያሳስብ ማስታወቂያ

የማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ አባላት ስብሰባ እንዲደረግ በማሳሰብ ለእያንዳንዱ የማህበሩ የአስተዳደር ቦርድ አባል የሚተላለፈው ማስታወቂያ አመቺ ነው ተብሎ በሚታመንበት በማናቸውም ዘይቤ ሊሆን ይችላል።

## አንቀጽ 25
## ማስታወቂያዎችን ስለማስቀረት

በማስታወቂያ እንዲገለጽላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ግለሰቦች በማስታወቂያ መጠራቱ ባለማስፈለጉ ቀሪ እንዲሆን መስማማታቸውን በፊርማቸው እስካረጋገጡ ድረስ፤ ማናቸውም ጉባኤ ሆነ ስብሰባ ያለአንዳች ማስታወቂያ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል VII ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ 26
## የሂሳብ ዓመት

1. የማህበሩ የሂሣብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## አንቀጽ 27
## የተጣራ ትርፍ

የትርፍ ድርሻን ለማህበርተኞቹ ለማከፋፈል የተጣራ ትርፍ አለ የሚባለው የማህበሩ ጠቅላላ ወጪ ተከፍሎ ማህበሩ ያስገኘው ትርፍ ሲኖር እና ባስገኘው ትርፍ መሠረት የሚከፈለው የትርፍ ግብር እና ለመጠባበቂያ መያዝ ያለበት ገንዘብ ከተነሳ በኋላ የሚተርፍ ገንዘብ ሲኖር ነው፡፡

## አንቀጽ 28
## የመጠባበቂያ ገንዘብ

1. ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ከማህበሩ ዋና ገንዘብ መጠን ጋር እኩል እስኪሆን ድረስ ማህበሩ ሊከፍለው የሚገባ የትርፍ ግብር ከተቀነሰ በኋላ በየዓመቱ ከሚገኘው ትርፍ ላይ አስር ከመቶ /10%/ እየተቀነሰ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተብሎ ይቀመጣል፡፡

2. ከዚህ በተጨማሪ ፣ ማህበሩ፣

ሀ/ የውል ጊዜው ላላለቀ ነገር ግን ለተሰበሰበ አረቦን፣

ለ/ ለተጠየቀ ነገር ግን ላልተከፈለ የመድን ውል ተቀባዮች ጥያቄ፣

ሐ/ በመድን ውሉ መሠረት የክፍያ ግዴታን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተፈጽመው ነገር ግን የክፍያ ጥያቄ ላልቀረበባቸው ጉዳዮች፣ እና

መ/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሚወስናቸው ተመሳሳይ ጉዳዮች፣ መጠባበቂያ ሂሳቦች ይይዛል፡፡

3. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሲወስን የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ ተጨማሪ የመጠባበቂያ ገንዘብ ያቋቁማል፡፡

4. ማናቸውም የመጠባበቂያ ገንዘብ ወለድ አያስገኝም፡፡

## አንቀጽ 29
## የተጣራ ትርፍን ስለማስታወቅና ስለአከፋፈሉ

1. ለባለአክሲዮኖቹ የሚከፈል የተጣራ ትርፍ በባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሊገለጽ ይችላል፡፡

2. ለባለአክሲዮኖች የሚከፈለው የተጣራ ትርፍ የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ፣ በንብረት ወይም ከማህበሩ አክሲዮኖች ሊሆን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 30
## ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫዎችና ሪፖርቶች

1. በእያንዳንዱ የማህበሩ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ የማህበሩን ንብረት የሚገልጽ የማህበሩ የንብረት ቆጠራ እና የማህበሩ ሀብት ዕዳ መግለጫ፣ የማህበሩ የሂሳብ ሚዛን፣ የማህበሩ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ ለጠቅላላ መድን ሥራው ፣ ለረጅም ጊዜ ለሚቆይ የመድን ንግድ ሥራው እና ለጠለፋ መድን የነበረውን የማህበሩን ሁኔታ እና ማህበሩ ያከናወናቸውን ተግባራት የሚያብራራ ጠቅላላ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

2. ከዚህ በላይ የተገለፀው ጠቅላላ ሪፖርትም ካለ የተጣራ ትርፍ የሚከፋፈልበት መንገድ እና ለማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ኃላፊዎች የተከፈለው ደመወዝ እና ልዩ ልዩ ወጪ ጭምር የሚገልጽ ሆኖ ይዘጋጃል፡፡

3. የዚህ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀስ አንድ /1/ የተገለፀው የማህበሩ የንብረት ቆጠራ፣ የማህበሩ ሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ የማህበሩ የሂሳብ ሚዛን፣ የማህበሩ የትርፍና የኪሳራ መግለጫ፣ የገቢና ወጪ ሒሳቦችና ጠቅላላ ሪፖርት ቅጂ የማህበሩ የሂሳብ ዓመት ካለቀበት አንስቶ በሶስት /3/ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፡፡

4. የማህበሩ ዋና ፀሐፊ በእያንዳንዱ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከዚህ በላይ ባለው በንዑስ አንቀጽ አንድ /1/ መሠረት የተዘጋጀውን የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሪፖርት ጉባኤው እንዲያፀድቀው፣ ውድቅ እንዲያደርገው ወይም እንዲያሻሽለው ለጉባኤው በንባብ ያሰማል፡፡

5. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ በፊት በሚገኘው ንዑስ አንቀጽ መሠረት በጉባኤው የፀደቀውን የማህበሩን የሂሳብ መግለጫዎች ቅጂ ሂሳቡ በፀደቀ በሰላሳ /30/ ቀኖች ውስጥ ለሚወስደው ተገቢ እርምጃ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመላክ ኃላፊነት አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ 31</u>
## <u>ገንዘብ ነክ ተግባራት</u>

ማንኛውም የማህበሩ ቼኮች ወይም በማህበሩ ላይ የሚቀርቡ የገንዘብ ይከፈል ጥያቄዎች እና የማህበሩ ገንዘብ ነክ ሰነዶች የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ በሚወክላቸው የማህበሩ ኃላፊዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ወይም ሰው ይፈርማሉ፡፡

## <u>አንቀጽ 32</u>
## <u>የማህበሩ መፍረስ</u>

1. የማህበሩ ባለአክሲዮን በሕግ መከልከል፣ መክሰር፣ ገንዘብ ማጣት ወይም መሞት የማህበሩን መፍረስ አያስከትልም፡፡
2. የሟች ባለአክሲዮን ወራሾች እንደምርጫቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የመሆን ወይም በመጨረሻው የማህበሩ የንብረት ዝርዝር መግለጫ መሠረት የወረሱአቸው አክሲዮኖች ዋጋ የመካፈል መብት አላቸው፡፡

3. ከዚህ በላይ ባለው በዚህ ንዑስ አንቀጽ  አንድ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ማህበሩ ከፈረሰ፣ሂሳቡ የሚጣራው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚሾመው በአንድ /1/ የሂሳብ አጣሪ ይሆናል፡፡

4. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በአንድ ድምጽ የሂሳብ አጣሪ መሾም ሳይችሉ ቀርተው የሂሳብ ልዩነት ካለ ግን ሂሳብ አጣሪው የሚሾመው የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ አጣሪውን ለመሾም ሥልጣን በሚኖረው ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

## **አንቀጽ 33**
## **ማህተም**

1. ማህበሩ የማህበሩ ስም፣ የተመዘገበበት ዓመት ምህረት እና "የማህበር ማህተም፣ ኢትዮጵያ" የሚሉ ቃላቶች በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች የተቀረጹበት ማህተም ይኖረዋል፡፡

2. የማህበሩን ማህተም ቅርጽ እያሰሩ በሚፈለገው ነገር ጉልህ ሆኖ እንዲወጣ በማድረግ በማተም ወይም በሌላ ሁኔታ በማባዛት የማህበሩን ማዕተም በተግባር ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

## **አንቀጽ 34**
## **ወሳኝ ቅጂ**

1. ሁለቱም የአማርኛና የእንግሊዝኛ የማህበሩ የመመሥራቻ ጽሑፍ ቅጂዎች የማህበሩ ኦፊስ የላዊ ሰነዶች ናቸው፡፡

2. በማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ እና የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅጂዎች መካከል ልዩነት ቢኖር ግን ወሳኙ የማህበሩ መመሥረቻ ጽሁፍ የአማርኛ ቅጂው ይሆናል፡፡